[redacted]

[redacted]

1. [redacted] ሁለት ትውልዶችን የሚያገናኝ የትውልድ ሐረግ ነው።

[redacted]

[redacted]

ዓመት ጊዜ ውስጥ ጋብቻው መፈጸም ይኖርበታል።

## አንቀጽ 14 የመተሚጨቱ መፍረስ

1. እጮኛው ወይም እጮኛይቱ መዘግየታቸውን ወይም

[redacted]

[redacted]
ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው።

**<u>አንቀጽ 22 በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ</u>**

ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 23 ከክልሉ ውጭ ስለሚፈፀም ጋብቻ</u>**

1. ሌሎች የጋብቻ አፈፃፀም ሕጎችን መሠረት በማድረግ ከኦሮሚያ ክልል ውጭ የተፈፀመ ጋብቻ የክልሉን ሕዝብ ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጋብቻቸውን ከክልሉ ውጭ ፈጽመው በጋብቻው ዘመን በክልሉ በሚኖሩ ሰዎች መካከል ክርክር የተነሣ እንደሆነ ሥልጣን ባለው የክልሉ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ መሠረት ይዳኛሉ፡፡
3. በዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ባልና ሚስት ስምምነታቸውን በጽሑፍ ሲያቀርቡ የክልሉ ፍርድ ቤት ጉዳያቸው በተጋቡበት ሕግ ወይም ባህል ወይም ኃይማኖት መሠረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡

**<u>አንቀጽ 24 ሌሎች የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች</u>**

በዚህ ክፍል ከተደነገጉት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ውጭ የተፈፀመ ማናቸውም ጋብቻ ውጤት አይኖረውም፡፡

**<u>ክፍል 2</u>**

**<u>ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 25 ፈቃድ</u>**

[redacted]

ጋብቻው በእንደራሴ ሊፈፀም ይችላል።

**አንቀጽ 30 መሠረታዊ ስህተት**

1. በስህተት በተገኘው ፈቃድ ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ

[redacted]

[redacted]

ሀ) የወለደች እንደሆነ ወይም ፣

ለ) ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር የሆነ እንደሆነ ወይም ፣

ሐ) እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም ፣

መ) በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ በብቸኝነት ለመኖር ስለተወሰነው ጊዜ የተደነ ገገው ተፈፃሚ አይሆንም::

## ክፍል 3
## ጋብቻ እንዳይፈጽም ስለመቃወም

### አንቀጽ 34 ስለመቃወም

ጋብቻ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈፀም የታሰበ ጋብቻ እንዳይፈፀም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል::

### አንቀጽ 35 መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈፀም መቃወም የሚችሉት ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው::

ሀ. በዕድሜ ምክንያት ሲሆን ወላጆች፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው፣

ለ. በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን የተጋቢዎቹ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወደላይ

[redacted]

[redacted] በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ይፈጸማል::

<u>አንቀጽ 40 (2) ጋብቻ ለመፈፀም ጥያቄ ስለሚቀርብበት ጊዜ</u>

ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው::

<u>አንቀጽ 41 (3) ጋብቻ የሚፈፀምበት ቀን ስለመወሰንና ስለማስታወቅ</u>

የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው እንደቀረበለት ከተጋቢቹ ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ ጋብቻው የሚፈፀምበትን ቀን ለመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል::

አንቀጽ 42 (4) የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት እና ጋብቻው መፈፀሙን ስለማስታወቅ

1. ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈፀማል::
2. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በቃለ መሐላ ያረጋግጣሉ::
3. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ የመሐላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ማስረዳት አለበት::
4. ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ያረጋግጣሉ::
5. ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው::
6. ከዚህ በላይ የተገለጹት ሥርዓቶች የተፈፀሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በሕጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል::

አንቀጽ 43 በሃይማኖት ሥርዓት ስለሚፈፀም ጋብቻ

1. በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሲፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት በዚህ ሕግ አንቀጽ 21 በተመለከተው መሠረት በተጋቢዎቹ ስምምነት እንደየሃይማኖቱ ይወሰናል::
2. በዚህ ሕግ ለማንኛውም ጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ለሚፈፀም ጋብቻም መሟላት አለባቸው::

አንቀጽ 44 በባህል ሥርዓት ስለሚፈፀም ጋብቻ

1. በባሕል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት በዚህ ሕግ አንቀጽ 22

[redacted]

ይኖረዋል::

<u>አንቀጽ 46 የጋብቻ መዝገብ ስለ ማደራጀት</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጋቢዎች ጋብቻውን ያላስመዘገቡ ቢሆንም እንኳን የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻ መፈፀሙን ያወቀ እንደሆነ የጋብቻ መዝገብ በሥልጣኑ ያደራጃል::
2. ይህ በሚሆንበት ጊዜ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹና እንደ ነገሩ ሁኔታ ምስክሮች ቀርበው በጋብቻው መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል::

<u>አንቀጽ 47 የጋብቻ መዝገብ ይዘት</u>

የጋብቻ መዝገብ የሚያመለክተው:-

ሀ. የተጋቢዎችን ሙሉ ስም ፣ የተወለዱበትን ቀንና ቦታ ፣ የመኖሪያ አድራሻቸውን፣

ለ. የምስክሮችን ሙሉ ስም ፣ የተወለዱበትን ቀንና ቦታ የመኖሪያ አድራሻቸውን፣

ሐ. ጋብቻው የተፈፀመበትን ሥርዓት ቀንና ቦታ ፣ እንዲሁም የተመዘገበበትን ቀን ይሆናል::

## ምዕራፍ አራት
## የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት

**አንቀጽ 48 የዕድሜ ሁኔታ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች በሆኑ ሰዎች መካከል የተፈፀመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል::
2. ሕጉ የሚጠይቀው የጋብቻ ዕድሜ ከተሟላ በኋላ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ መወሰን አይቻልም::

**አንቀጽ 49 የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና**

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይፈጸም የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ የተፈጸመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል::

**አንቀጽ 50 በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ**

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤት ሳይፈቅድ ጋብቻ ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል::
2. የተከለከለው ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ክልከላው ከቀረበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ ሊቀርብ አይችልም::

3. ጋብቻው እንዲፈርስ በአሳዳሪው የሚቀርበው ጥያቄ ጋብቻው መፈፀሙን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ክልከላው ከቀረ በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

<u>አንቀጽ 51 በኃይል ተግባር የተፈፀመ ጋብቻን ስለማፍረስ</u>

1. ማንኛውም ሰው ተገዶ ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።
2. ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የኃይል ሥራው ከቀረበት ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

<u>አንቀጽ 52 በስህተት ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻን ስለማፍረስ</u>

1. ማንኛውም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት በመነሳት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።
2. ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ መሳሳቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

<u>አንቀጽ 53 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ አልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም።

**አንቀጽ 54 የክብር መዝገብ ሹም ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ የሚያስከትለው ውጤት**

ጋብቻውን ያስፈጸመው የክብር መዝገብ ሹም በዚህ ሕግ በአንቀጽ 39 መሠረት ሥልጣን አልነበረውም በማለት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ለመወሰን አይቻልም::

**አንቀጽ 55 የሥነ ሥርዓት አለመጠበቅ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (6) የተመለከቱት ሥርዓቶች አልተጠበቁም በማለት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም::

## ምዕራፍ አምስት

## የጋብቻ ውጤት

### ክፍል 1

### ጠቅላላ

**አንቀጽ 56 ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ስለ መሆኑ**

1. በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት የተፈፀመ ጋብቻ ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል::
2. በዚህ ረገድ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሃይማኖት ወይም በባህል በታዘዙት ሥርዓቶች መሠረት የተፈፀመም ቢሆን ልዩነት አይደረግበትም::

**አንቀጽ 57 የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም**

የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በዕውነት መፈፀሙ ወይም ተፈጽሟል ተብሎ መገመቱ ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊ አይደለም::

**አንቀጽ 58(1) የጋብቻ ውል**

1. ተጋቢዎቹ ጋብቻቸው ያፈሩትን ንብረት በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈፀማቸው

በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸው በሚፈፀምበት ዕለት በውል መወሰን ይችላሉ፡፡

2. እንዲሁም ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት የሚኖራቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ውል መወሰን ይችላሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ተጋቢዎቹ የሚያደርጎቸው ውሎች አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

<u>አንቀጽ 59 (2) የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት</u>

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገውን የጋብቻ ውል እርሱ ራሱ ካልፈፀመውና ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡

2. በሕግ የተከለከለ ሰው የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል፡፡

<u>አንቀጽ 60 (3) የውሉ ፎርም</u>

የጋብቻ ውል በጽሑፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡

<u>አንቀጽ 61 (4) የውሉ ሰነድ ስለሚቀመጥበት ቦታ</u>

1. የጋብቻ ውሉ አንድ ቅጅ በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል፡፡

2. ተጋቢዎች ወይም ከተጋቢዎች አንዱ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም በፍርድ ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ በአንዱ የተፈቀደላቸው ሰዎች የውሉን ሰነድ ለማየት ይችላሉ፡፡

<u>አንቀጽ 62 (5) ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን</u>

1. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም፡፡

2. እንዲሁም ተጋቢዎቹ ባሕልን ወይም ሃይማኖትን ወይም የአንድን አገር ሕግ በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል [redacted]

[redacted]

1. ከባልና ከሚስቱ አንዱ ከጋብቻው በፊት ከሌላ የወለዳቸውን ልጆች መልካም አስተዳደግ በሚመለከት በራሱ አሳብና መሪነት የፈቀደውን ውሳኔ ለማድረግ ሙሉ መብት ይኖረዋል።

2. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም::

## አንቀጽ 69 አብሮ መኖር

1. ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ::
2. ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው::
3. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም::

## አንቀጽ 70 የመኖሪያ ሥፍራን ስለመወሰን

ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ሥፍራ በጋራ ይወስናሉ::

## አንቀጽ 71 በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር

1. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማት ይችላሉ::
2. ስለዚህ ጉዳይ የተደነገገውን ስምምነት መለወጥ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው አስቦ ሊሰርዘው ይችላል::

## አንቀጽ 72የመተማመን ግዴታ

ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው::

## ክፍል 3

## ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

## አንቀጽ 73 የባልና ሚስት የግል ሀብት (1) ያለግብይት የተገኙ ንበረቶች

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀራሉ::

**አንቀጽ 74 (2) በግብይት የተገኙ ንብረቶች**

1. ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤት ሲያፀድቀው ብቻ ነው።

**አንቀጽ 75 የግል ሀብትን ስለማስተዳደር (1) መሠረቱ**

1. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል።
2. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ሊያዝበት ነፃነት አለው።

**አንቀጽ 76 (2) የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን**

1. ባልና ሚስት አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአስፈፈላጊነቱ እንዲያዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው አኳኋን ንብረት የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ስለንብረቱ አስተዳደር ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።

**አንቀጽ 77 (3) ስለውክልና ሥልጣን**

ከተጋቢዎች አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ለሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል።

**አንቀጽ 78 የባልና ሚስት የጋራ ሀብት**

1. ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎችና ውጤቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።

2. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል፡፡
3. በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ቃል በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 79 የሕግ ግምት

1. አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
2. የግል ንብረት መሆኑን ሦስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ይኸው ንብረት የግል ነው በማለት በሶስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡት አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 80 ስለባል ሚስት ገቢ (1) መደበኛ የገቢ አስተዳደር

1. ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ይቀበላሉ፡፡
2. ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡
3. ከባልና ከሚስት አንደኛው ሲጠይቅ ሌላኛው ተጋቢ ያገኘውን የገቢ መጠን የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 81(2) ልዩ ሁኔታ

1. ከባልና ከሚስት አንዱ ገቢውን ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልለት ሥልጣን ለመስጠት ሙሉ ነፃነት አለው፡፡

2. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ጠያቂነት የአንደኛውን ገቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል::
3. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከባልና ከሚስት የአንደኛው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል::

<u>አንቀጽ 82 የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር</u>

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ::
2. ከባልና ከሚስት አንዱ ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱን ሲገፈፍ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማ ስተዳደር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ሀብቱን የማስተደደሩን ተግባር ያከናውናል::

<u>አንቀጽ 83 የማስታወቅ ግዴታ</u>

ከተጋቢዎች አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት::

<u>አንቀጽ 84 (1) የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ</u>

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው::

ሀ. የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ፣ ለማከራየት፣ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማኛቸውም ሁኔታ በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ፣

ለ. ዋጋቸው ከብር 500 ( አምስት መቶ ) በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ የጋራ ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሰነዶችን ለመሸጥ ለመለወጥ በመያገር ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ፣

ሐ. ከብር 100 (አንድ መቶ) በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለሌላ ሰው በስጦታ ለማ ስተላለፍ፣

መ. ከብር 500 ( አምስት መቶ ) በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን።

<u>አንቀጽ 85 (2) የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት</u>

1. አንደኛው ተጋቢ ከዚህ በላይ የተመለከተውን ድንጋጌ ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ ይችላል።
2. ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

<u>አንቀጽ 86 የባልና ሚስት ዕዳ</u>

1. ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሀብት የግል ሀብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸው ይከፈላል።
2. ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ከጋራ ሀብታቸው የጋራ ሀብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት ይከፈላል።

<u>አንቀጽ 87 ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር ዕዳ</u>

የሚከተሉት ዕዳዎች ለትዳር ጥቅም እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ናቸው፣

ሀ. ለባልና ለሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት የተገቡ ዕዳ ዎች፣

ለ. ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተደረጉ ወጪዎች ፣

ሐ. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂ አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ ፍርድ ቤት የተቀበለው ሌላ ዕዳ፣

**አንቀጽ 88 የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን**

ተጋቢዎች የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደ የአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው::

**አንቀጽ 89 በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረጉ ውሎች**

ባልና ሚስቱ ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚያ ደርጎቸው ውሎች ፍርድ ቤት ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም::

## ምዕራፍ ስድስት
## በጋብቻ ውስጥ የሚነሡ ክርክሮችን ስለመወሰን
### ክፍል 1
### ጋብቻ ለመፈፀሙ ወይም የሚፀና ጋብቻ ለመኖሩ ስለሚቀርብ ክርክር

**አንቀጽ 90 የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ**

ጋብቻ በዚህ ሕግ ምዕራፍ 3 እና 4 በተደነገገው መሠረት ጋብቻ ለመፈፀሙ ወይም የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩን አጣርቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ተጋቢዎች ጥያቂያቸውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ::

**አንቀጽ 91 የፍርድ ቤት ሥልጣን**

1. ጋብቻ ለመፈፀሙ ወይም የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ የሚነሣውን ክርክር አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው::

2. ፍርድ ቤቱም በአንቀጽ 90 መሠረት የሚቀርብለትን ጥያቄ በዚህ ህግ አንቀጽ 92 - 95 መሠረት በሚቀርቡለት ማስረጃዎች እያጣራ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል።
3. የዚህ አንቀጽ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ በፍቺ ክርክር ውስጥ ሊነሡ ለሚችሉ የጋብቻ መፈፀም ወይም የሚፀና ጋብቻ መኖር ጥያቄዎችም እንደየአግባቡ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

<u>አንቀጽ 92 ጋብቻ ለመፈፀሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ (1) የጋብቻ የምስክር ወረቀት</u>

ጋብቻ መፈፀሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈፀመበት ዕለት ወይም ከዚያ በኋላ በሕጉ መሠረት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት ወይም የጋብቻውን መዝገብ የተረጋገጠ ግልባጭ በማቅረብ ነው።

<u>አንቀጽ 93 (2) የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ</u>

1. የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ የቀረ ወይም መዝገቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈፀሙን በጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ ጋብቻ ለመፈፀሙ አሳማኝና በቂ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አንድ ሰው በራሱና ከእርሱ ጋር ጋብቻ አለኝ የሚለው ወገን ጋር ጋብቻ መፈጸሙን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ግምት ጋብቻው አለመፈፀሙን ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይቻላል።

## ክፍል 2
## ክፍቺ በመለስ ያሉ ክርክሮችን ስለመወሰን

### አንቀጽ 94 በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች

በዚህ ሕግ አንቀጽ 90 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ባል ወይም ሚስት ወይም ሁለቱም በአንድነት ከፍቺ በመለስ የሆኑ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን አስመልክተው አቤቱታቸውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ::

### አንቀጽ 95 የፍርድ ቤቱ ሥልጣን

1. ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 94 መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት ባልና ሚስቱን በተናጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር አለመግባባቱን በስምምነት መፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል::
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ሞክሮ ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት በስምምነት እንዲጨርሱ ከሁለት ወር ያልበለጠ ጊዜ በመወሰን ያሰናብታቸዋል::
3. በሽማግሌዎቹ በሚቀርብ የማስማሚያ ሃሳብ ያልተስማማ ወገን አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል::
4. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በሽማግሌዎቹ የተሰጠውን የማስማሚያ ሃሳብ ሊያፀና፣ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል:: የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::

## ምዕራፍ ሰባት
## የጋብቻ መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት
## ክፍል 1
## ጠቅላላ

### አንቀጽ 96 በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው

ጋብቻው የተፈጸመበት ሥርዓት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የጋብቻው መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት በተመለከተ ምንም ዓይነት ልዩነት አይደረግበትም::

## አንቀጽ 97 ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፣

ሀ. ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ ወይም

ለ. ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን ወይም

ሐ.የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ፣

## አንቀጽ 98 ስለፍቺና ስለ ፍቺ ውጤቶች የመወሰን ስልጣን

የፍቺ ስምምነትን የማጽደቅ ወይም ፍቹን የመወሰን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 112 በተደነገገው መሠረት የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።

## ክፍል 2
## በስምምነት ስለመፋታት

## አንቀጽ 99 ፍቺ በስምምነት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

ጋብቻ በስምምነት እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችለው፣ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ነው።

## አንቀጽ 100 በስምምነት ለመፋታት ስለሚቀርብ ጥያቄ

1. ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት የወሰኑ እንደሆነ የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሑፍ ለፍርድቤት በማቅረብ ፍቺው እንዲፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ፣ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት አይፈቀድላቸውም።

ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ሞክሮ ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ጉዳያቸውን በዕርቅ እንዲጨርሱ ይጠይቃቸዋል፡፡
3. ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌ አማካይነት በዕርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከሦስት ወር ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያስናብታቸው ይችላል፡፡
4. የፍቺ አቤቱታው እንደቀረበ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ፣ ስለል ጆቻቸው አጠባበቅ፣ ስለሚኖሩበት ስፍራና ስለአናኗራቸው እንዲሁም ስለንብረታቸው አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
5. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው መሠረት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን እንዲሁም የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

<u>አንቀጽ 106 ስለዕርቅ (1) አስታራቂ ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ባልና ሚስት ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ በወሰኑ ጊዜ አመቺ ሆኖ በሚያገኙት መንገድ አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን በመምረጥ ሽማግሌ እንዲ መርጡ ከተነገራቸው ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎቹን ስም ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሽማግሌዎች ስም ዝርዝር ስቀርብለት ወይም ሽማግሌዎቹ እንደቀረቡ ወዲያውኑ መዝገቦ ዕርቅ የሚከናወንበትን የመፍትሔ አቅጣጫ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ በመስጠት ወይም እንዲደርሳቸው በማድረግ የዕርቁ ወይም የዕርቁ ሙከራ ውጤት በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ያዛል::

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የዕርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለመመርመርና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ማዘዝ ይችላል::

<u>አንቀጽ 107 (2) ስለተጨማሪ ጊዜ</u>

ከዕርቅ ሙከራው ሂደት አኳያ ባልና ሚስት ያለመግባባታቸውን በዕርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ የሚል ግምት ያለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 106 በተመለከተው ጊዜ ሳይገደብ ከአንድ ወር ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት የዕርቅ ሙከራው እንዲቀጥል ሊያዝ ይችላል::

<u>አንቀጽ 108 (3) የአስታራቂ ሽማግሌዎች ኃላፊነት</u>

1. አስታራቂ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሳባቸውን እንዲተውና ጉዳያቸውን በመግባባት እንዲጨርሱ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው::

2. አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩ ከፍቺ በመለስ ሊፈታ እንደማይችል የተረዱ እንደሆነ ተጨማሪ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ስለደረሰበት ውጤት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው::

3. አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍቺ በመለስ በማግባባት ለመፍታት ከመጣር አልፈው ባልና ሚስቱን የሚመለከት

ማናቸውንም ትዕዛዝም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አይኖራቸውም።

<u>አንቀጽ 109 (4) የሪፖርት አለመቅረብ</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 106 እና 108 መሠረት አስታራቂዎቹ ሪፖርት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል።
2. መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ጉዳያቸውን በዕርቅ አለመጨረሳቸውንና ሪፖርት በወቅቱ ያልቀረበበትን ምክንያት በመግለጽ ጉዳያቸው እንዲንቀሳቀስላቸው የጠየቁ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥያቄያቸው ተገቢ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን በመክፈት በሕጉ መሠረት የራሱን ውሳኔ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው መዝገቡን የመዝጋት ውሳኔ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው አዲስ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም።

<u>አንቀጽ 110 (5) ፍቺና የፍቺ ውጤቶችን ስለመወሰን</u>

1. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን ሁሉ አድርጎ ጥረቱ ውጤት ያላስገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ሪፖርት ከደረሰው ወይም እንደሁኔታው ለተጋቢዎቹ የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል።
2. በዚህ ክፍል መሠረት ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ፍቺው ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲስማሙ ባልና ሚስቱን ይጠይቃቸዋል።
3. ባልና ሚስቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረትለመስማማት ያልፈለጉ ወይም ለመስማማት

ምክረው ስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም በሽማግሌዎች ወይም ፍርድ ቤቱ በሚሾማቸው ባለሞያዎች አማካይነት ወይም አመቺ መስሎ በሚታየው በማናቸውም ዘዴ የፍቺውን ውጤት ይወስናል።

4. ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ውጤት በሚወስንበት ጊዜ ከተጋቢዎች ያንደኛው ጥፋት የሆነ ከባድ ምክንያት መኖሩን ወይም ያለመኖሩን ከግምት በማስገባት ይሆናል።
5. የፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወስንበት ጊዜ ውሳኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው።
6. ፍርድ ቤቱ ፍቺውን አስቀድሞ በመወሰን የፍቺውን ውጤት በተመለከተ የሚሰጠውን ውሳኔ እንደሁኔታው ከፍቺ በኋላ ከ6 ወር ሳልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል።

## አንቀጽ 111 ስለ ካሳ

1. ከባልና ከሚስት ባንዱ የተፈጸመውና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ የተገኘው ጥፋት በሌላው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ በዳዩ ሳደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ይወስናል ።
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከጋራ ንብረት በካሣ መልክ ያንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን ወይም ሙሉውን በደል ለተፈፀመበት ወገን ሊሰጥ ይችላል።
3. መፋታቱ የተወሰነው የሁለቱም ወገኖች ጥፋት ባልሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከላይ የተመለከቱት ቅጣቶች በሁለቱም ላይ አይፈፀምባቸውም።

## ክፍል 4
## የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት

## አንቀጽ 112 የባልና ሚስትን ሀብት በስምምነት ስለማጣራት

1. በዚህ ሕግ ስለካሣ ክፍያ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጋብቻው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የፈረሰ እንደሆነ

ባልና ሚስቱ የጋብቻቸው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ይጣራል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ሌላ ስምምነት የሌለ ወይም በሕግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የባልና ሚስት ሀብት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይጣራል።

## አንቀጽ 113 የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ

1. ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረቱን መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል።
2. ከባልና ሚስቱ አንደኛው የግል ሀብቱ የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑንና ከዚሁ ግብይት የተገኘውም ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከዚህ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ የማንሳት መብት ይኖረዋል።
3. ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁለቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን እንደየአስተዋጽኦዋቸው ሊደርሳቸው የሚችለውን ያህል የማንሳት መብት ይኖራቸዋል።

## አንቀጽ 114 ስለካሳ

1. በዚህ ሕግ መሠረት የጋራ ንብረቱን ወይም የሌላኛውን ተጋቢ ንብረት በብቸኝነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ በፈፀማቸው ድርጊቶች ምክንያት ወይም ከብልሹ አስተዳደር የተነሳ ወይም የካሳ ጠያቂውን መብት በማታለል ድርጊቱ የጎዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተበዳዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ተጋቢ የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ሦስት ዓመት በፊት የሆነ እንደሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።

<u>አንቀጽ 115 ያለአግባብ ስለመበልጸግ</u>

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር ከባልና ሚስት የአንደኛው የግል ሀብት ከሆነ ንብረት የሌላኛው የግል ሀብት ወይም የጋራ ሀብታቸው ያለአግባብ መበልጸጉን ያስረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ካሳ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል።

<u>አንቀጽ 116 የዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማስከበር</u>

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው ዕዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል ይሆናል።

<u>አንቀጽ 117 የጋራ ሀብትን ስለማከፋፈል</u>

ከዚህ በላይ የተመለከቱትና የባልና ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለማከፋፈል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል።

<u>አንቀጽ 118 የባልና ሚስት ሀብት በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ</u>

1. በመሠረቱ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሀብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው አኳኋን እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል።

3. የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

<u>አንቀጽ 119 ለማከፋፈል አዳጋች ስለሆኑ ንብረቶች</u>

1. ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል።
2. ስለአሻሻጡ ሁኔታ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ ቀርተው አንደኛው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ ይሆናል።

<u>አንቀጽ 120 ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ከባልና ከሚስት ስለሚጠየቅ ዕዳ</u>

1. ጋብቻው ከፈረሰና የባልና ሚስት ሀብት ከተከፋፈለ በኋላ የሚጠየቅ ዕዳ በጋራ መከፈል የነበረበት በሆነ ጊዜ ስለዕዳው አከፋፈል ሁለቱም በየድርሻቸው መጠን ተጠያቂ ይሆናሉ።
2. ዕዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ በሆነ ጊዜ የዕዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለዕዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ ይሆናል።

## <u>ክፍል 5</u>
## <u>የክርክሮች ሂደትና አወሳሰን</u>

<u>አንቀጽ 121 ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ሕግ</u>

በዚህ ሕግ የተመለከቱት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ሕግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች

እና የክልሉ መንግስት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

አንቀጽ 122 የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው

1. ጋብቻው የፈረሰው በፍቺ ባይሆንም የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት በዚህ በምዕራፍ 7 ክፍል 4 የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ::
2. በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ በሕይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሳ እንደሆነ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት በዚህ ምዕራፍ ክፍል 4 የተደነገጉት እንደዚሁ እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ::

አንቀጽ 123 የጋብቻ ሁኔታዎች መጓደል

በዚህ ሕግ ምዕራፍ ሁለት ከአንቀጽ 48 እስከ 55 በተመለከተው መሠረት የጋብቻ ሁኔታዎች ከመጓደላቸው የተነሣ የጋብቻ መፍረስ በሚወሰንበት ጊዜ ፍርድ ቤት መፍረሱ የሚያስከትለውን ውጤት በርትዕ ይወስናል::

አንቀጽ 124 የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ
ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ያስችላል::

አንቀጽ 125 ስለ ውሳኔ አሰጣጥ
ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍቺ በሚወሰንበት ጊዜ የተጋቢዎችን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ

ዝርዝር ጉዳዩችን ከመተችት በመቆጠብ ፍቺውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሳኔው ላይ ሊያሰፍር ይችላል::

<u>አንቀጽ 126 ስለ ይግባኝ</u>

ፍርድ ቤቱ ፍቺ መወሰኑን ብቻ መሠረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም::

<u>አንቀጽ 127 የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሳኔ</u>

1. ፍርድ ቤቱ ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወስን ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ ስለቀለባቸውና ባጠቃላይ ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት::
2. ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የወላጆች የገቢ የዕድሜ ፣ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆቹን ዕድሜ ጥቅማቸውና ፍላጐታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል::
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ተቃራኒ ውሣኔ የሚያሰጥ የተረጋገጠ ምክንያት በሌላኛው ወገን እስካልቀረበ በቀር ዕድሜአቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑ ሕፃናት ከእናታቸው ጋር እንዲቆዩ ይደረጋል::
4. በዚህ አንቀጽ መሰረት ስለልጆች አጠባበቅና እንክብካቤ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታ ለውጥ ምክንያት በማድረግ በሚቀረበው ጥያቄ ማሻሻል ወይም መለወጥ ይችላል::

## <u>ምዕራፍ ስምንት</u>
## <u>ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር</u>

<u>አንቀጽ 128 (1) ትርጓሜ</u>

ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈጽሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው::

አንቀጽ 129 (2) ማብራሪያ

1. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው፡፡
2. ለሶስተኛ ወገኖች እንደተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አይደለም፡፡
3. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀማቸው ብቻ በሁለቱ መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

አንቀጽ 130 የጋብቻ ዝምድና የማያስከትል ስለመሆኑ

1. ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በወንድየውና በሴቲቱ የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትየዋና በወንድየው የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዳችም የጋብቻ ዝምድና አያስከትልም፡፡
2. ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለ ጊዜ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለ ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 131 የጋራ ኑሮ ወጪዎችን ስለመሸፈን

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው ፡፡

አንቀጽ 132 ስለ ጋራ ሀብት

1. የንብረትአስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉትን ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነት ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ፡፡

2. ተቃራኒ ማስረጃ አስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖሩ ወንድና ሴት የሚገሯቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ የተፈሩ ሀብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ።
3. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገቧቸው ዕዳዎች አብረው የሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም የግንኙነቱ የተወለዱ ልጆችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ ዕዳዎች ሲሆን ለዕዳዎቹ አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ኃላፊዎች ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ 133 የጋራ ንብረት ስለሚያስከትለው ውጤት</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 132 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት በጋራ ሀብት የሚፈጠርበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር የሶስተኛ ወገን ዕዳ አከፋፈልና ንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ሕግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራት ሂደት የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።( አንቀጽ 112 - 120)

<u>አንቀጽ 134 የልጆች መወለድ</u>

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱት ልጆች ተወላጅነታቸው የሚረጋገጠው በዚህ ሕግ ስለመወለድ በተባለው ምዕራፍ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

<u>አንቀጽ 135 የግንኙነት መቋረጥ</u>

1. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማንኛውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ።
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 132 ስለጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሳ እንዲከፍል አይገደድም።

<u>አንቀጽ 136 የግንኙነቱ ማስረጃ</u>

1. ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የግንኙነቱ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል።

2. አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳን በሕግ የተጋቡ ባይሆኑም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ሁኔታ መኖሩን አንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ናቸው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።
4. ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግ ግምት ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ግንኙነት ያለመ ኖሩን በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል።

<u>አንቀጽ 137 የክርክሮች ሂደትና አወሳሰን(1) ሥልጣን ስላለው አካል</u>

በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

<u>አንቀጽ 138 (2) ተፈፃሚነት ስለሚኖረው ሕግ</u>

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 121 እስከ 127 የክርክሮችን ሂደትና አወሳሰን በሚመለከት የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደአ ግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ግንኙነት ውስጥ በሚነሡ ክርክሮችም እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ 139 ጋብቻ ሳይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች</u>

1. ከጋብቻ ሥርዓት ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጪ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት አይኖራቸውም።

2. በዚህ ሕግ ስለ ጉዲፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከእንደዚህ ያለ ግንኙነት የተወለዱ ልጆች ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት ህጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም።

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ስለ መወለድ
## ክፍል 1
## አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ
### ንዑስ ክፍል 1
### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 140 የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው**

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር አባትነትና እናትነትን ስለማወቅ የተመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም።

**አንቀጽ 141 ስለእናትነት**

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው በመሆንዋ ብቻ እናትነትዋ ይታወቃል።

**አንቀጽ 142 ስለ አባትነት**

1. ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይታወቃል።
2. አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያትም አባትነት ሊታወቅ ይችላል።
3. በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔም አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል።

### ንዑስ ክፍል 2
### አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

**አንቀጽ 143 ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ**

በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው።

አንቀጽ 144 የግምቱ አጠቃላይነት

1. ከልጁ ጋር ያለው የእናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ ቢሆንም በአንቀፅ 143 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።
2. የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳን ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።
3. ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል።

አንቀጽ 145 እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ

1. ጋብቻው ከተፈፀመ ከ180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል።
2. ለዚህተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

አንቀጽ 146 የባልየው መጥፋት

በዚህ ሕግ ስለአባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች በሕግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለመኖሩ ወሬ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ300 ቀናት በኋላ ለተወለደ ልጅ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 147 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር

1. ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባት በዚሁ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው።
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 144 እና 145 ስለግምቱ አጠቃላይነትና እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው የሕግ ግምትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ንዑስ ክፍል 3
## ልጅነትን ስለመቀበል

**አንቀጽ 148(1) መሠረቱ**

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ሊታወቅ ያልቻለ እንደሆነ አባትየው ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ሊታወቅ ይችላል::

**አንቀጽ 149 (2) ትርጓሜ**

አንድ ሰው አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን አምኖ በመቀበል ቃሉን የሰጠ እንደሆነ የልጁ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል::

**አንቀጽ 150 (1) ሥርዓት (ፎርም)**

አንድ ሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለፅ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሑፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለፅ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል::

**አንቀጽ 151 ስለውክልና**

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው::
2. ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል::
3. በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት ሊሰጥ ይችላል::

**አንቀጽ 152 የአባትየው መሞት**

የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል::

አንቀጽ 153 እናት የተቀባዩን አባትነት ስላለማመንዋ

1. የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጁ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም፡፡
2. የልጁ እናት የሞተች ወይም ፈቃድዋን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ ወደላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሳዳሪ ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 154 ስለ ልጁ ለአካለ መጠን መድረስ

ልጅነትን የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው፡፡

አንቀጽ 155 እምኖ የመቀበሉ ሁኔታ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 152 እና 153 የተመለከቱት ሰዎች የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን

3. ልጁ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ብቻ ነው፡፡ የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾቹ በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 158 ስለማፍረስ**

1. ልጅነትን ለመቀበል የተነገረ ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል፡፡
2. ልጁ ነው ብሎ ከተቀበለ ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነትን የመቀበሉ ድርጊት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 159 አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው**

ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ ካልተደረገ በስተቀር ሌላ ሰው ልጁ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## ንዑስ ክፍል 4
## በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ

**አንቀጽ 160 (1) በፍርድ ስለሚነገር አባትነት**

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ እንደሆነና ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ ይችላል፡፡

ሀ. ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፣

ለ. ሆን ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም አገባሻለሁ ሲል የተሰፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የማሳት ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፣

ሐ. አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፉና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ሲኖሩ፣

መ. በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በህግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ እንደሆነ፣

ሠ. አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ ወይም በማስተማር ወይም በማሳደግ ላይ እንደአባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ፣

<u>አንቀጽ 161 (2) አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ክስ</u>

ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን አባትነት በፍርድ እንዲነገር የሚቀርብ ክስ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ባሉ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም፣

ሀ. በሌላኛው ሰው የልጁ አባት ላለመሆኑ በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀምዋ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

ለ. አባት ነው የተባለው ሰው በህግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ በመጥፋቱ ወይም በአደጋ ምክንያት አባት ሊሆን የማይችልበትን ሁኔታ ሲያረጋግጥ፣

ሐ. አባት ነው የተባለው ሰው በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ የልጁ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን ሲያረጋግጥ፣

<u>አንቀጽ 162 ሌላ ሁኔታ ስላለመኖሩ</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ 160 ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊታወቅ አይችልም።

## ክፍል 2

## አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት

**አንቀጽ 163 አባትነትን ስለመወሰን (1) መሠረቱ**

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በማድረግ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጁ አባትነት በህግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል::

**አንቀጽ 164 (2) ሥርዓት (ፎርም)**

1. የአባትነት ውሳኔ የሚያሰጠውን ስምምነት ሶስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል፣
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የልጁን እናት ቃል መስማት ይገባል::

**አንቀጽ 165 የሕግ ግምት**

ስለ አባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ሁለት የህግ ግምቶች በመከተል ይፈጸማል፣

ሀ. ጋብቻ ሳይፈጽም እንደ ባል ከሚኖር ሰው ይልቅ ህጋዊው ባል ይመረጣል::

ለ. ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል::

**አንቀጽ 166 (1) አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ**

1. ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከተፈጸመ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተጀመረ አንስቶ በ210 ቀናት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ባልየው ወይም ከሴትዮዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው የልጁ

አባት እኔ ነኝ ለሚል ሌላ ሰው በስምምነት አባትነቱን ሊያስተላልፍለት ይችላል።

2. እንዲሁም ልጁ ከጋብቻው መፍረስ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተቋረጠበት ቀን በኋላ 210 ቀኖችን አሳልፎ ተወልዶ እንደሆነ ባልየው ወይም እንደባል አብኖ የኖረው ሰው ከዚህ በላይ የተነገረው መብት ይኖረዋል።

<u>አንቀጽ 167 (2) ሥርዓት (ፎርም)</u>

1. በስምምነት የሚደረግ አባትነትን የማስተላለፍ ድርጊት ሶስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያጸድቀው ይገባል።
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የእናቲቱ ቃል መሰማት አለበት።

<u>አንቀጽ 168 ስለወኪልነት</u>

1. በዚህ ክፍል የተመለከቱትን ስምምነቶች አካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ያልተከለከሉ ባለጉዳዮች ራሳቸው መጨረስ አለባቸው።
2. ስምምነቱን ሌላ ሰው እንዲያከናውንለት ማድረግ የሚቻለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥል ጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።

<u>አንቀጽ 169 ቃልን ስለመሻር</u>

አባትነትን በስምምነት የመወሰን ወይም የማስተላለፍ ድርጊት ሊሻር አይችልም።

<u>አንቀጽ 170 ስለማፍረስ</u>

1. ልጅነትን ለመቀበል የተደረገ ስምምነት በኃይል ድርጊት የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።
2. ልጅ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስ ተቀር

ልጅነትን የመቀበሉ ስምምነት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

ክፍል 3
ስለ ልጅነት ማስረጃ

አንቀጽ 171 የልደት ምስክር ወረቀት

አባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰው ልጅነት የእገሌ ልጅ ነው የሚል የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረ ጋገጣል።

አንቀጽ 172 የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚ ቀርብ ማስረጃ

የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት ይረጋገጣል፣

አንቀጽ 173 የልጅነት ሁኔታ መኖር (1) ትርጓሜ

አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው።

አንቀጽ 174 ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ ስለማስረዳት

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እን ደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጁ ነው ሲል የህግ ግምት ይወስዳል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመ ለከተውን ግምት ልጁ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል።

አንቀጽ 175 ተወላጅነትን ለማስረዳት ስለሚቀርብ ክስ

1. የልጅነት ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።
2. ተወላጅነትን የማረጋገጥ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም

3. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያ ደርጉ ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚ መነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 176 ክስን ስላለመቀበል

ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ የሚፈልገው ሰው ስለመወለዱ ከተሰጠው የልደት ምስክር ወረቀት ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ ከሌላ ሰው ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም።

## አንቀጽ 177 ስለ ክስ

1. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ልጁ ወይም አሳዳሪው ወይም ወራሾቹ ናቸው።
2. እንደዚሁም የልጁ አባት ወይም እናት ነን የሚሉት ሰዎች ክስ ለማቅረብ ይችላሉ።

## አንቀጽ 178 ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ

1. ልጁ በህይወት እስካለ ድረስ ተወላጅነቱን ለማረ ጋገጥ ክስ ለማቅረብ ይችላል።
2. የልጁ ወላጆች ወይም አሳዳሪዎች ልጁ አካለመጠን ባልደረሰበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም።
3. ልጁ ሃያ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

## አንቀጽ 179 ስለ ተከሳሽ

1. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክሱን ያቀረበችው እናት ነኝ የምትል ሴት በሆነች ጊዜ ክሱ የሚቀርበው በልጁ ላይ ነው።

2. ሆኖም ክሱ የቀረበው በሌላ ሰው ሲሆን ክሱ የሚቀርበው እናት ነች በተባለችው ወይም በወራሾችዋ ላይ ነው::

## ክፍል 4

## በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለ መካድ

### ንዑስ ክፍል 1

### በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር

**አንቀጽ 180 መሠረቱ**

በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት ይችላል::

**አንቀጽ 181 ክስን ስለመቀበል**

1. በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይ ችልም::
2. በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀ በል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው ተገባ ራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው::

**አንቀጽ 182 ክስን ስላለመቀበል**

ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት ምስክር ወረቀትና ከዚህ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነቱ ላይ ለመከራከር ፈቃድ አይሰጥም::

**አንቀጽ 183 ስለ ክስ**

1. በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሳበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ይመሰረታል::

2. የልጁን እናት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የልጁን አባት ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል 2
## ስለ መካድ

**አንቀጽ 184 መሠረቱ**

በአባት በኩል ያለውን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 185 ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስላለመኖር**

**(1) መሠረቱ**

የልጁ አባት ነህ ተብሎ በሀግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ300ኛውና በ180ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 186 (2) የሕግ ግምት**

1. ከሁለቱ አንዱ ባቀረበው የመፋታት ጥያቄ መሠረት ወይም በሁለቱ መካከል በተደረገው የመለያየት ስምምነት ምክንያት ባልና ሚስቱ በእውነት ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ በመካ ከላቸው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዳልተደረገ ይገ መታል፡፡
2. ስለዚህ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው ማስረጃ በማናቸውም ምክንያቶች ቢሆን ይሰማል፡፡

**አንቀጽ 187 አባት ለመሆን ስለአለመቻሉ (1) መሠረቱ**

በሕግ የልጁ አባት ነህ የተባለው ሰው የዚሁ ልጅ አባት ሊሆን አለመቻሉን በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ ይችላል፡፡

አንቀጽ 188 (2) ክስን ለመቀበል ስለመቻል

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተ ቀር ሊቀርብ አይችልም::
2. ፈቃዱም የሚሰጠው ፍርድ ቤት ክሱን እንዲቀበል የሚያደርገው በቂና አስተማማኝ ከሆነ መረጃ የሚ መነጭ የህሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው::

አንቀጽ 189 (3) ስለ ህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች

1. የህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች የሚባሉት ልጅህ ነው ከተባለው ሰው አባትነት ጋር የማይስማሙ ለመሆናቸው በሳይንስ እውቀት ተለይተው የማታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ሲሆኑ ይችላሉ::
2. እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሴቲቱ በሰውየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሳድር አኳኋን የልጁን መወለድ ወይም እርግዝናዋን ከሰውየው ከደበቀችው ነው::

አንቀጽ 190 (4) ስለ ሴሰኝነት (በባል ላይ ስለሚደረግ ዝሙት) ወይም ስለ እናቲቱ ማመን

እናቲቱ በባልዋ ላይ ያደረገችው የሴሰኝነት (የዝሙት) ሥራ ወይም ልጁ የሌላ ሰው ለመሆኑ የምትሰጠው የእምነት ቃል ብቻ እንደ ከባድ ምክንያት ሊቆጠሩ አይችሉም::

አንቀጽ 191 ስለ ከሳሽ

1. የእኔ ልጅ አይደለም ብሎ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው::
2. በዚህ ጉዳይ በተለይ እናቲቱ አባት ነኝ ባዩ ዐቃቤ ሕግ ወይም ልጁ ራሱ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም::

አንቀጽ 192 በፍርድ የተከለከለ ሰው

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤትን አስፈቅዶ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል::

2. እንዲሁም በፍርድ የተከለከለው ሰው አሳዳሪ ይህንኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ በፍርድ በተከለከለው ሰው ስም ሆኖ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል::

<u>አንቀጽ 193 ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ (1) መሠረቱ</u>

1. የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት::
3. እናትነት የተወሰነው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበ ክስ ሲሆን የመካድ ክስ የሚቀርበው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ክስ የሚወስን የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ ነው::

<u>አንቀጽ 194 (2) ልዩ ሁኔታ</u>

1. በሕግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል::
2. ተወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አባትና እናቱ እነዚህም የሌሉ እንደሆነ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ አንዱ መብቱን ሊሰራበት ይችላል::
3. ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ የተባለውን መብት ማንኛውንም ሌላ ወራሽ ወይም ወኪልን ሳይጨምር ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ ሊሰራበት ይችላል::

<u>አንቀጽ 195 ክስን ስላለመቀበል</u>

ባልየው በጽሁፍ በሰጠው ፈቃድ መሠረት ልጁ በሰው ሰራሽ ዘዴ የተፀነሰ ለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም::

አንቀጽ 196 ስለ ተከሳሾች

1. የመካድ ክስ በልጁ ላይ እርሱም ሞቶ እንደሆነ በወራሾቹ ላይ ያቀርባል።
2. የልጁን እናት በሚቀርበው ክስ ውስጥ እንድትገባ ማድረግ ያስፈልጋል።
3. ልጁ አካለመጠን ያልደረሰ ከሆነ ፍርድ ቤት በተለይ ለዚህ ጉዳይ የመረጠው ሞግዚት ወኪል ይሆነዋል።

ምዕራፍ አሥር

ስለ ጉዲፈቻ

አንቀጽ 197 ስለጉዲፈቻ ዝምድና (1) መሠረቱ

በሕዝቡ ልማድ መሠረት ወይም በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል።

አንቀጽ 198 (2) ውጤቱ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 199 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል።

አንቀጽ 199 (3) ልዩ ሁኔታ

1. 1.ጉዲፈቻ የጉዲፈቻውን ስምምነት በግልጽ የተቃወሙትን ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን ወይም ወደጐን የሚቆጠሩ ዘመዶችን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ተቃውሞ ስምምነቱ በፍርድ ቤት መጽደቁ በታወቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር አይፀናም።

አንቀጽ 200 የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

1. የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠበቀ ይቆያል።

2. የጉዲፈቻ ልጅየው ሚስት/ባል እና ተወላጆችም ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የዝምድና ግንኙነት ይኖራቸ ዋል፡፡
3. በቀደምት ቤተሰቦቹና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ለጉዲፈቻ ቤተ ሰቦቹ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

<u>አንቀጽ 201 የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ</u>

1. ዕድሜው ከ25 ዓመት ያላነሰ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል፡፡
2. ጉዲፈቻ አድራጊዎች ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ የአንዳቸው ዕድሜ 25 ዓመት የሞላ ከሆነ በቂ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው ሰው ፍርድ ቤቱ የልጁን ጥቅም በጥሩ ሁኔታ ለመጠበቅ ይችላል ብሎ ካመነበት ጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 202 የጉዲፈቻ ልጅ ዕድሜ</u>

ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ያልወጣ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 203 ያገባ ሰው ስለሚያደርገው ጉዲፈቻ</u>

1. ጉዲፈቻ አድራጊው ያገባ በሚሆንበት ጊዜ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር ጉዲፈቻ ማድረግ አይ ቻልም፡፡
2. የጉዲፈቻው ልጅ የጉዲፈቻ አድራጊው ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
3. እንዲሁም ከባል እና ከሚስት አንደኛው ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

<u>አንቀጽ 204 የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ስለማድረግ</u>

1. የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይቻላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ልጁ በተወለደ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን በገዛ ፈቃድዋ ብቻ ለመሠረዝ ትችላለች::

<u>አንቀጽ 205 ስለ ጉዲፈቻው አድራጊው ልጆች</u>

1. ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ ጉዲፈቻ ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም::
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ 211(1) መሠረት ጉዲፈቻ ከማጽደቁ አስቀድሞ ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ በጉዲፈቻ ልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት::

<u>አንቀጽ 206 አንድ ልጅ ከአንድ በላይ ጉዲፈቻ አድራጊ ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ</u>

1. ባልና ሚስት ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ልጅ ለብዙ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ሊሆን አይችልም::
2. ጉዲፈቻ አድራጊው የሞተ እንደሆነ ግን አዲስ ጉዲፈቻ ማድረግ ይቻላል::
3. ልጅየው የባልና ሚስት የጉዲፈቻ ልጅ ከሆነና ከባልና ሚስቱ አንደኛው የሞተ እንደሆነ በሕይወት ካለው ሰው ጋር የሚጋባው አዲስ ተጋቢ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርገው ይችላል::

<u>አንቀጽ 207 ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች</u>

የጉዲፈቻው ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል ይደረጋል::

<u>አንቀጽ 208 የጉዲፈቻው ልጅ ወላጆች ፈቃድ</u>

1. የልጁ አባትና እናት በሕይወት ያሉና የታወቁ ከሆነ ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል::

2. ከወላጆቹ አንደኛው የሞተ የጠፋ የማይታወቅ እንደሆነ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ሌላኛው ወላጅ ፈቃዱን ይሰጣል::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከወላጆቹ አንዱ ፈቃዱን ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነና የልጁ ዕድሜ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ያንደኛውን ወላጅ ፈቃድና የልጁን አስተያየት በመጠየቅ ጉዲፈቻውን ሊያፀድቀው ይችላል::
4. ልጁ ፈቃዱን ለመስጠት የሚችል ወደላይ የሚቆጠር ወላጅ የሌለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለልጁ ያለውን ጠቃሚነት ግምት ውስጥ በማስገባት ጉዲፈቻውን ሊያ ፀድቀው ይችላል::

<u>አንቀጽ 209 ስለመንግሥት ወይም የግል ዕጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች</u>

1. የመንግሥት ወይም የግል ዕጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች እያሳደጉት ያሉትን ማንኛውንም ልጅ ለጉዲፈቻ አድራጊዎች በስምምነት ለመስጠት ይችላሉ::
2. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቋሞች አንድን ልጅ በስምምነት ከመስጠታቸው በፊት የሕፃናትን ደህንነት ለመከ ታተል ሥልጣን ለተሰጠው የመንግሥት አካል ስለልጁ ማንነት ተቋሙ በምን ሁኔታ እንደተረከበውና ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም መግለጫ ማቅረብ አለባቸው::

<u>አንቀጽ 210 ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን</u>

1. ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው አካል ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ፣ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በማጠናቀርና በመመርመር ስምምነቱ ቢደረግ ለልጁ ጠቃሚነት ይኖረዋል ሲል አስተያየቱን ካልሰጠ በስተቀር የጉዲ ፈቻውን ስምምነት ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው አይችልም::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ለልጁ ጠቃሚነት አይኖረውም ሲል የገመተ እንደሆነ የባለሥልጣኑን አስተያየት ባለመቀበል ስምምነቱን ላያፀድቀው ይችላል።

3. ፍርድ ቤቱ ከባለሥልጣኑ የቀረበለት መረጃ በቂ መስሎ ያልታየው እንደሆነ አዲስ ምርመራ በማከናወን ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት ባለሥልጣኑን ለማዘዝ እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊ መስሎ የሚታያቸውንና በእጃቸው የሚገኘውን መረጃ እንዲያቀርቡ ወይም እንደአስፈላጊነቱ የምስ ክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ለማዘዝ ይችላል።

<u>አንቀጽ 211 የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1. በዘልማድ ወይም በውል የተገባ የጉዲፈቻ ስምምነት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይ ኖረውም።
2. ፍርድ ቤቱ ጉዲፈቻ ከማጽደቁ አስቀድሞ በወሳኝ መልኩ ለልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
3. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 209 እና 210 የተመለከቱትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ አነጋገር እንደ ተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፣

   ሀ. ልጅየው ስለጉዲፈቻ ስምምነቱ ያለውን አስተያየት፣

   ለ.አስቀድሞ ፈቃዱን ያልሰጠ ከሆነም የአሳዳ ሪውን አስተያየት፣

   ሐ. ጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ለማሳደግና ለመንከባከብ ያለውን ብቃት፣

   መ. ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ልጅየው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያድግበት ሁኔታ አለመኖሩን፣

ሠ. ጉዲፈቻ አድራጊው እንደልጁ አድርጐ እንደ ሚያሳድገውና አላግባብ መጠቀሚያ እንደማያደ ርገው ለመገመት የሚያስችል መረጃ መኖሩን።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በፊደል ተራ (ሠ) የተመለከተውን በሚያጣራበት ጊዜ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

<u>አንቀጽ 212 የጉዲፈቻ ስምምነት የማይሰረዝ ስለመሆኑ</u>

1. የጉዲፈቻ ስምምነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከተው ሁኔታ ውጪ ሊሰረዝ አይችልም።
2. ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጁ በማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም ባርነትን በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ ገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሠማራ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሠረዝ ይችላል።

<u>አንቀጽ 213 ጉዲፈቻ እንዲሰረዝ አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

1. የጉዲፈቻው ልጅ ራሱ የሕጻናትን ደኅንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ወይም በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከ ተው አንቀጽ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ ጉዲፈቻው እንዲሰረዝ አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ መንቀጽ (1) መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ጉዲፈቻ አድራጊውን ከማስቀ ረቡ በፊት ለአቤቱታው ምክንያት ናቸው የተባሉት መረ ጃዎች እውነት ሆነው ቢገኙ ጉዲፈቻውን ለማፍረስ በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## ቀለብ የመስጠት ግዴታ

### አንቀጽ 214 ስለግዴታው ይዘት

በዚህ ሕግ አንቀጽ 215 ድንጋጌዎች መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማውን በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፡ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን እንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት አለበት ፡፡

### አንቀጽ 215 ግዴታው በእነማን መካከል ስለመሆኑ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖረው በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች ወይም በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ነው፡፡
2. እንዲሁም በወንደማማቾች እና እህትማማቾች መካከል ቀለብ የመስጠት ግዴታ ይኖራል፡፡

### አንቀጽ 216 ግዴታው ስለሚቀርበት ሁኔታ

ጋብቻ የፈረሰው በሞት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ከጋብቻ መፍረስ በኋላ ቀሪ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 217 ቀለብ ተቀባዩ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ

ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚህ ሰው ወደላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ሕይወት ወይም ንብረት ላይ የወንጀል ተግባር የፈጸመ ወይም ለመፈጸም የሞከረ እንደሆነ ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል፡፡

### አንቀጽ 218 ግዴታው እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታዎች

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለውና በችግር ላይ የወደቀ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ 219 ስለግዴታው አፈጻጸም

1. በመሠረቱ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚፈጸመው ቀለብ ሰጪው ለቀለብ ተቀባዩ የቀለቡን ገንዘብ በመስጠት ነው።
2. የቀለቡ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማመዛዘን ነው።

አንቀጽ 220 ውሳኔውን ማሻሻል የሚቻል ስለመሆኑ

ቀለብ ሰጪው ወይም ተቀባዩ የሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስለቀለቡ መጠን ወይም ስለቀለብ ተቀባዩ መኖሪያ የተሰጠውን ውሳኔ በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይቻላል።

አንቀጽ 221 ቀለቡ ስለሚከፈልበት ቦታ

ቀለቡ የሚከፈለው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ይሆናል።

አንቀጽ 222 (1) የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ

1. ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ ሊተላለፍ ወይም ሊያዝ አይችልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ለዕርዳታ ለተቋቋሙ ድርጅቶች ሊተላለፍ ይችላል።
3. እንዲሁም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ለቀለብ ተቀባዩ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያቀረቡ ሌሎች ሰዎችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 223 (2) የቀለብ ገንዘብ የማይጠራቀም ስለመሆኑ

ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር የቀለቡን ገንዘብ መቀበል ካለበት ቀን ጀምሮ በተከታዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ያልተቀበለው ወይም ሳይጠይቀው የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመው ቀለብ እንዲሰጠው መጠየቅ አይችልም።

አንቀጽ 224 ቀለብ ተቀባዩን በቀለብ ሰጪው ቤት ለማኖር ስለመቻል

1. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ ተቀብሎ በማስቀመጥ ቀለብ የመስጠት ግዴታውን ሊፈጽም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የነገሩን የአካባቢ ሁኔታዎች በመመልከት ተገቢ መስሎ የታየውን ይወስናል፡፡
3. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ እንዳያስቀምጥ ምንጊዜም ቢሆን አይገደድም፡፡

አንቀጽ 225 ስለቀለብ ሰጪዎች ብዛት (1) መሠረት

ለቀለብ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ የሆኑ እንደሆነ ቀለብ ተቀባዩ ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው ሊጠይቀው ይችላል፡፡

አንቀጽ 226 (2) ስለ አቤቱታ

1. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሆነው ከእነርሱ መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ቀለቡን የከፈሉ እንደሆነ ሳይከፍሉ የቀሩት ድርሻቸውን እንዲከፍሏቸው ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተካሳሾቹ ያላቸውን ሀብትና ከከሳሽ ጋር ያላቸውን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ደረጃ በማመዛዘን ተከሳሾቹ የቀለቡን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊወስንባቸው ይችላል፡፡

አንቀጽ 227 (3) ለቀለብ ሰጪዎች የሚሰጥ የከፋይነት ተራ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 215 መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ቅደም ተከተል፡

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ ፣ ባል ወይም ሚስት
ለ) በሁለተኛ ደረጃ ፣ ተወላጆች እንደየደረጃቸው
ሐ) በሦስተኛ ደረጃ ፣ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እን ደየደረጃቸው፡
መ) በአራተኛ ደረጃ ፣ ወንድማማችና እህትማማቾች
ሠ) በአምስተኛ ደረጃ ፣ የጋብቻ ተወላጆች እንደየደረ ጃቸው፡፡
ረ) በስድስተኛ ደረጃ ፣ የጋብቻ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላ ጆች እንደየደረጃቸው፡፡

## አንቀጽ 228 በጋራ ቀለብ ሰጪዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት

1. የጋራ ቀለብ ሰጪዎች እርስ በእርሳቸው ስለአላቸው ግንኙነት ለጋራ ቀለብ ተቀባያቸው ከእነርሱ መካከል አንድ ቀለቡን እንዲሰጠው በማለት የሚፀና ስምምነት ለማድረግ ይችላሉ፡፡
2. ቀለብ ተቀባዩ ስምምነቱን ወዶ የተቀበለ እንደሆነ ይህንን ስምምነት የማያከብርበት ከባድ ምክንያት ካልተገኘ በስተቀር ቀለቡን ከሌሎቹ ቀለብ ሰጪዎች መጠየቅ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 229 ስለ ጉዲፈቻ ልጅ ልዩ ሁኔታ

1. የጉዲፈቻ ልጅ ባል ወይም ሚስትና የቀጥታ መስመር ተወላጆች የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመዶች ቀለቡን መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ካልተገኙ በስተቀር የሥር ወላጆቹን ቤተዘመዶች ቀለብ ለመጠየቅ አይችሉም፡፡
2. የቀደምት ቤተሰቦቹ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከዘመዶቻቸው አንዱን ለመጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በስተቀር በጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ ሊጠ ይቁት አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 230 ስለ ሥርዓተ ቀብር ወጪ

1. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለዚሁ ለተባለው ሰው ሥርዓተ ቀብር የወጣውንም ወጪ ለመክፈል ይገደዳል፡፡

2. ይህን ወጪ ያደረገው ሰው፣ ወጪውን እንዲተካለት ቀለብ ሰጪውን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 231 ልዩ ስምምነቶች</u>

ልዩ ስምምነቶችን በማድረግ በዚህ ምዕራፍ የተጻፉትን ድንጋጌዎች ለመለወጥ አይፈቀድም፡፡

## <u>ምዕራፍ አሥራ ሁለት</u>

## <u>አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች</u>

## <u>ክፍል 1</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

<u>አንቀጽ 232 ትርጓሜ</u>

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ሰው ነው፡፡

<u>አንቀጽ 233 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ስለመልካም አስተዳደጉና ደህንነቱ ጉዳይ በአንድ አሳዳሪው እየተጠበቀ ይቆያል፡፡
2. ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና በአጠቃላይ የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት በሞግዚቱ ይወከላል፡፡
3. በሕግ በግልጽ ለተመለከቱ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ሕጋዊ ድርጊቶችን ለመፈፀም አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ 234 የዕድሜ ማስረጃ</u>

1. የአንድ ሰው ዕድሜ የሚረጋገጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው፡፡
2. የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ ዕድሜውን በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላሉ በሚባሉ ሰነዶች ወይም ከሁለት ያላነሱ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ዕድሜውን ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 235 ውሳኔ ሰጪ አካላት መከተል ስላለባቸው መርህ**

በዚህ ምዕራፍ መሠረት በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች ሁሉ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን ይኖርባቸዋል::

## ክፍል 2

## አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች

**አንቀጽ 236 የወላጆች ሥልጣን**

አባትና እናት ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ አካለመጠን ላለደረሱት ልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ሥልጣን ይኖራቸዋል::

**አንቀጽ 237 ከወላጆቹ አንዱ ብቁ አለመሆን**

1. ከወላጆቹ አንዱ የሞተ፣ ችሎታ ያጣ፣ የተገቢነት መብት ያጣ ወይም የቤተሰብ አስተዳዳሪነት መብቱ የታገደ እንደሆነ የአሳዳሪነትና ሞግዚትነት ሥልጣኑን ይዞ የሚቆየው አንደኛው ወገን ብቻ ይሆናል::
2. እንዲሁም የልጁ አባት ያልታወቀ በሆነ ጊዜ የዚህን ሥልጣን ሥራ የምትፈፅመው እናቱ ብቻ ትሆናለች::

**አንቀጽ 238 የልጁ አባትና እናት መፋታት**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 99 መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ሲፋቱ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት በተመለከተ በስምምነት ይወስናሉ::
2. በማናቸውም የፍቺ ሁኔታ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ባልና ሚስቱ በስምምነት ሊወስኑ ካልቻሉ ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስለልጆቹ አሳዳሪና ሞግዚትም አብሮ ይወስናል::

**አንቀጽ 239 በኑዛዜ ቃል የተመረጠ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት**

**(1) መሠረቱ**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በህይወት ያለው ወላጅ ከጊዜ ሞቱ በኋላ ልጁን የሚያስተዳድር ወይም ለልጁ

ሞግዚት የሚሆነውን ሰው በመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ለመምረጥ ይችላል::

2. እንዲሁም የአሳዳሪውን ወይም የሞግዚቱን ሥልጣን ለመወሰንና የአሳዳጊነቱን የሥራ አመራር ሥልጣን በተወሰነ ሁኔታ ብቻ ለመስጠት ይችላል::

<u>አንቀጽ 240 (2) አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለመሾም የሚፈፀም ግዴታ</u>

አባት ወይም እናት በህይወት ሳለ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የአሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራ ያካሂድ የነበረ ካልሆነና በዚሁም ጊዜ በገዛ ፈቃድ ሥልጣኑን አውቆ የተወ ከልሆነ በስተቀር በዚህ ሕግ አንቀጽ 239 ለአባት ወይም ለእናት የተሰጠውን መብት አይኖረውም::

<u>አንቀጽ 241 (3) ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የሚያስገድድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለ አሳዳሪው ወይም ስለሞግዚቱ አባቱ ያደረጉትን ውሳኔ ፍርድ ቤት ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል::

<u>አንቀጽ 242 የልጅን አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ዘመዶች (1) ሊከተሉት የሚገባ ቅደም ተከተል</u>

አንድ ልጅ አባትና እናት የሌለው እንደሆነና ከሁለቱ በመጨረሻ የሞተው ወላጅ በሚገባ ሁኔታ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሳያደርግለት ቀርቶ እንደሆነ ለልጁ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በሕጉ መሠረት የሚመረጡና ይህ ሥልጣን የሚሰጣቸው በዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ናቸው::

ሀ. የልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች

ለ. እነዚህ በሌሉ ጊዜ አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድሞች ወይም እህቶች

ሐ. እነዚህ በሌሉ ጊዜ የልጁ አጎት ወይም አክስት::

<u>አንቀጽ 243 (2) ይህ ቅደም ተከተል ስለሚለወጥበት ሁኔታ</u>

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሥልጣን በሚሰጠው ሰው ምትክ ለልጁ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ

ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥልጣን ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል።

2. ይህም ጥያቄ መቅረብ የሚገባው ቅደም ተከተሉ ለሚመለከታቸው ዘመዶች ሲሆን ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ይቀርባል።
3. ጥያቄው መቅረብ ያለበት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥልጣን መያዙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል።
4. ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መሠረት የሚሆነው የልጁ ደህንነትና ጥቅም ሲሆን ይገባል።

አንቀጽ 244 በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች መታጣት

1. ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ በልጁ አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ይህ ሥራና ሥልጣን ፍርድ ቤት ለመረጠው ሰው ሊሰጥ ይችላል።
2. ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ ለመወሰን የልጁ ዘመድ በሆነ ወይም ባልሆነ ያገባኛል ባይ በሚቀርብ ጥያቄ ሊመሰረት ይችላል።
3. የህፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካልም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

አንቀጽ 245 የፍርድ ቤት ምርጫ (1) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች

ፍርድ ቤት ለልጁ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሆን የሚመርጠውና ይህን ሥልጣን የሚሰጠው የልጁ የቅርብ የሥጋ ዘመድ የሆነን ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለውንና በተቻለም መጠን ይህን ሥራ ለማከናወን ችሎታና ፈቃደኛነት ያለውን ሰው ነው።

አንቀጽ 246 የበጐ አድራጐት ድርጅት

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነቱን ሥልጣን ለዚህ ዓይነት ጉዳይ ለተቋቋመ የበጐ አድራጎት ድርጅት ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 247 ተመሳሳይ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ለተዘፋ‌ት ድንጋጌዎች አፈፃፀም አንድ ሰው በሕግ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባሮችን ለማከናወን የማይችል እንደሆነ እንደሌለ ይቆጠራል::

አንቀጽ 248 የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ መታወቂያ

1. በመሠረቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን ሥልጣን ተሰጥቶት የልጁን አሳዳሪነት የተቀበለው ሰው ሞግዚቱም ነው::
2. የነገሩ ሁኔታ ተቃራኒ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በህይወት ያለው አባት ወይም እናት ወይም ፍርድ ቤት ለልጁ የሚሾሙት ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ሁለቱንም ሥልጣን እንደያዘ ይቆጠራል::

አንቀጽ 249 ለአባትና ለእናት የተሰጠ መብት

አባት ወይም እናት ጉዳዩ ጠቃሚ መስሎ የታያቸው እንደሆነ የልጃቸውን የአሳዳሪነት ሥልጣን ራሳቸው ይዘው ሞግዚት ለመሾም ይችላሉ::

አንቀጽ 250 ለፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን

ፍርድ ቤት የልጁን አሳዳሪና ሞግዚት የመሾም ሥልጣን በያዘበት ጊዜና ይህን ለማድረግ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ከአሳዳሪው በተጨማሪ ሌላ ሞግዚት ለመሾም ይችላል

አንቀጽ 251 ምትክ ሞግዚት (1) በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት

1. በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል የጥቅም ግጭት የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤት አካለመጠን ሳልደረሰው ልጅ ምትክ ሞግዚት ይሾምለታል::

2. ምትክ ሞግዚት የሚመረጠው በሞግዚቱ ወይም ወደ ላይ ከሚቆጠሩ የልጁ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በአንዳቸው ጥያቄ አቅራቢነት ነው፡፡

<u>አንቀጽ 252 (2) አካለመጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት</u>

1. አካለመጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል የጥቅም ግጭት የተፈጠረ እንደሆነና የነዚህም ተጠሪ ወኪል አንድ የጋራ ሞግዚት ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡(አንቀጽ 251)
2. የጥቅም ግጭቱ የሚፈታውም በሞግዚቱና በምትክ ሞግዚት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ 253 የሥራ አጀማመር</u>

1. የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የሚጀመረው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በሕግ መሠረት ወይም በፍርድ ውሳኔ ተመርጠው እንደተሾሙ ወዲያውኑ ነው፡፡
2. ሆኖም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ከማወቁ በፊት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥራውን ሳይጀምር ለደረሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ሊጠየቅ አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ 254 ሥራው የግዴታ ስለመሆኑ</u>

የአሳዳሪነትን ወይም የሞግዚትነትን ሥራዎች እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመው ሰው ሥራውን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡

<u>አንቀጽ 255 ሥራው እንዲቀርለት የሚቀርብ ጥያቄ</u>

1. አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባርን ማከናወን በራሱ ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይ ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ሥራው እንዲቀርለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2. እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ከተሰጠው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራው እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

## አንቀጽ 256 ሥራው እንዲቀርለት በሕግ አግባብ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት

በዚህ ሕግ መሠረት ለአሳዳሪነት ወይም ለሞግዚትነት ስለሚመረጡ ሰዎች የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በአሳዳሪነት ወይም በሞግዚትነት እንዳይሾሙ ወይም እንዲሻሩ ጥያቄ ካቀረቡና ይህም ጥያቄ የራሳቸውን ልጆች የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲሰሩ አይገደዱም።

ሀ. ዕድሜው ስድሳ አምስት ዓመት የሞላው ሰው

ለ. በውትድርና የተሰማሩ ሰዎች።

## አንቀጽ 257 ለጊዜው ሥራውን የማከናወን ግዴታ

1. የልጁ አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ችግር ያደርስብኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ ይህ ኃላፊነት እንዲወገድለት የሚጠይቅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት በዚህ ሥራ ሌላ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ተወክሎ ሥልጣኑን እስከሚረከብ ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት።
2. እንዲሁም በሹመቱ ላይ ተቃውሞ የተነሳበት አሳዳሪ ወይም ሞግዚትም ተመሳሳይ ግዴታ ይኖርበታል።

## አንቀጽ 258 ስለ ሥራው መቅረት

1. የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ሥራ ቀሪ የሚሆነው የሚጠበቀው ልጅ የሞተ እንደሆነ ወይም አካለመጠን በደረሰ ጊዜ ወይም ከሞግዚት አስተዳዳር ነፃ በወጣ ጊዜ ነው።
2. እንዲሁም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ወይም ብቁ ያለመሆኑ ሲገለጽ ወይም ከሥራው ሲሻር ቀሪ ይሆናል።

3. አዲስ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲሾምለትም የቀድሞዎቹ ተሿሚዎችኃላፊነት ያበቃል::

<u>አንቀጽ 259 ችሎታ ማጣት (1) አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ</u>

የራሱን ልጆች በሚመለከት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የአሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ችሎታ የለውም::

<u>አንቀጽ 260 (2) በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች</u>

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማከናወን አይችልም::
2. ይህን ሥራ ያከናውን የነበረ አንድ ሰው ችሎታ ያጣ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገለጸ እንደሆነ የዚህ ሰው ሞግዚት በሕግ መሠረት የተከለከለውን ሰው ሥራ ተረክቦ በምትክነት ማካሄድ ለሚገባው ሰው ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት::
3. እንዲህ ያለ ሰው የሌለም እንደሆነ በፍርድ የተከለከለው ሰው ምትክ እንዲደረግለት ሞግዚቱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለበት::

<u>አንቀጽ 261 ብቁ ስላለመሆን</u>

1. አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ብቁ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ለመወሰን የሚችለው የወንጀል ተግባር በመፈጸሙ የግል ነፃነትን የሚከለክል የእስራት ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን ነው::
2. ፍርድ ቤት የዚህን ዓይነት ቅጣት በአንድ ሰው ላይ በሚወስንበት ጊዜ ነገሩ ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለዚህ ሥራ ብቁ አለመሆኑን ጭምር ለመወሰን ይችላል::

አንቀጽ 262 (1) የአሳዳሪው መሻር

1. አካለመጠን ሳልደረሰ ልጅ አሳዳሪው እንዲሆን የተሾመ ሰው ልጁ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ሳያገኝ ወይም ከሞራል ጋር የሚስማማ የአእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ሳያደርግለት የቀረ እንደሆነ አሳዳሪው እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል::
2. ይህንንም ውሳኔ ለመስጠት አሳዳሪው የሚኖርበትን የአካባቢ ሁኔታና ጊዜውንም መመርመርና መሠረት ማድረግ አስፈላጊ ነው::
3. በተለይም ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ለመሻር የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወንጀል መስራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህንንም ወንጀል የፈፀመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረ ገብ ትምህርት ለማግኘት ባለመቻሉ የሆነ እንደሆነ ነው::

አንቀጽ 263 (2) የሞግዚት መሻር

አካለመጠን ሳልደረሰ ልጅ ሞግዚት የሆነ ሰው እንዲሻር ፍርድ ቤት የሚወስነው ሞግዚቱ የልጁን ንብረትና ሀብት በመጥፎ ሁኔታ ያስተዳደረና አጠባበቁም በቂ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ልጁን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የሰጠው ሰው ወይም አካል የሰጠውን መመሪያና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሳይጠብቅና ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም ዕዳ ለመክፈል ያለመቻሉ በፍርድ ውሳኔ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው::

አንቀጽ 264 (3) የወላጆች መሻር

1. የልጁ አባት ወይም እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ ከልጃቸው አሳዳሪነት ወይም ሞግዚ ትነት ስራቸው እንዲሻሩ መወሰን ሲያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል::

2. ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ በቱሻረው ወገን ጠያቂነት በማንኛውም ጊዜ እንደገና ሊመረምረው ይችላል::

<u>አንቀጽ 265 (4) ሥነ ሥርዓት</u>

1. አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር የሚቀርበው ጥያቄ በማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ባይ ወገን ወይም በዐቃቤ ሕግ በኩል ሊቀርብ ይችላል::
2. ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን በመሻር ከመወሰኑ በፊት በርሱ በኩል ያለውን ሀሳብ ሊያዳምጠው ይገባል::
3. ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ሲያከናውን በልጁ ደህንነት ወይም ሀብት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል::

<u>አንቀጽ 266 የፍርድ ቤት ኃላፊነት</u>

1. ፍርድ ቤት አንድን ሰው አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ለመሾም ሲመርጥ ወይም የተሾመውን ከሥራው ሲሽር ከውሳኔው በፊት በተቻለ መጠን ከልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹን ሀሳብ ሊያዳምጥ ይችላል::
2. አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያለውን ሀሳብ ሊያዳምጥ ይችላል::
3. ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ሲሰጥ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የማይጓደልበትን አሠራር ብቻ መከተል እንጂ የቀረቡለትን ሀሳቦች የመቀበል ግዴታ አይኖርበትም::

<u>አንቀጽ 267 ሥራው ያለ ክፍያ የሚከናወን ስለመሆኑ</u>

1. የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ የሚከናወነው ማናቸውም ዋጋ ሳይከፈልበት በነፃ ነው::

2. ሆኖም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሥራውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚጠይቀው የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት ይችላል።
3. ይህም አበል አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሀብት ገቢ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሀብት ሊወሰድ አይችልም የአበሉም ልክ ከጠቅላላው የሀብት ገቢ ሲሶ ሊበልጥ አይችልም።

<u>አንቀጽ 268 የሥራው አካሄድ የግል ስለመሆኑ</u>

1. የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የግል ጠባይ የያዘ ስለሆነ ሥራውን የሚያከናውነው ራሱ እንጂ ለአሳዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ወራሾች ሊተላለፍ አይችልም።
2. ወራሾቹ በኃላፊነት የሚጠየቁት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በፈፀመው የሥራ አካሄድ ጉድለት ብቻ ነው። ይህም በውርስ ሕግ መሠረት ይወሰናል።

<u>አንቀጽ 269 የወራሾች ግዴታ</u>

1. የአንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ወራሾች አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ እንደሞተ ወዲያውኑ በዚህ ሕግ አንቀጽ 242 በተመለከተው መሠረት ለሟቹ ምትክ ሊሆን የሚገባውን ሰው ለማስታወቅ ግዴታ አለባቸው።
2. የዚህ ዓይነት ሰው የሌለ እንደሆነ በሟቹ ምትክ የሚመረጠው ሰው እንዲሾም ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለባቸው።
3. የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱትን ግዴታዎች እስኪወጡ ድረስ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅም ሆነ ለሌላ ሦሥተኛ ወገኖች ኃላፊዎች ሆነው ይቆያሉ።

<u>አንቀጽ 270 የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ</u>

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሳዳሪነቱን ወይም ሞግዚትነቱን የሚያስረዳለት ጽሑፍ እንዲሰጠው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ፍርድ ቤትን ለመጠየቅ ይችላል።

<u>አንቀጽ 271 ከሞግዚት ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ</u>

ሞግዚትን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ክፍል ሦስት
## የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን
## ንዑስ ክፍል አንድ
## አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ

**አንቀጽ 272 አሳዳሪው የመንግሥት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ ስለመቻሉ**

አሳዳሪው ከዚህ በታች በተመለከቱት አንቀጾች የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል አግባብነት ያላቸውን የመንግሥት ተቋሞች እገዛ ሊጠይቅ ይችላል::

**አንቀጽ 273 አካለመጠን ስላልደረሰ ልጅ መኖሪያ ቦታ**

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ መኖሪያ ቦታ ይወስናል::
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ያለአሳዳሪው ፈቃድ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ሊተው አይችልም::
3. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታትቶ የሄደ እንደሆነ አሳዳሪው ወደ መኖሪያ ቦታው እንዲመለስ ሊያስገድደው ይችላል::

**አንቀጽ 274 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ጤና አጠባበቅ**

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤንነት ሁኔታ ይከታተላል::
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሲታመም ከህመሙ እንዲፈወስ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል::

**አንቀጽ 275 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግ**

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ይመራል::
2. አሳዳሪው አካለመጠን ሳልደረሰው ልጅ መልካም አስተዳደግ ተገቢነት ያለውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል::

**አንቀጽ 276 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት**

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል::

2. ሆኖም አሳዳሪው በቂ ምክንያት ሳይኖረው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም::

<u>አንቀጽ 277 አጠቃላይ እና የሙያ ትምህርት የመስጠት ግዴታ</u>

አሳዳሪው አካለመጠን ሳልደረሰው ልጅ ዕድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ሥልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት::

<u>አንቀጽ 278 አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ (1) መሠረቱ</u>

1. አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅየው ጥቅም ያውላል::
2. አሳዳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም::

<u>አንቀጽ 279 (2) ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሳዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት በዚህ ሕግ አንቀጽ 278(2) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል::
2. ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ አስተዳደግና ለትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሳዳሪው እንዲሰጠው ያደርጋል::
3. ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ሥራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ይደረጋል::

<u>አንቀጽ 280 (3) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥራው ስለሚያገኘው ገቢ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜው ከ 14 ዓመት በላይ ሲሆን ከሥራው የሚያገኘውን ገቢ እራሱ ይቀበላል::

2. ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሳዳሪው ከሰጠ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሊጠቀምበት ሙሉ ነፃነት አለው።

<u>አንቀጽ 281(4) በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፉ ሀብቶች</u>

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ ሰው ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ አሳዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዳያውለው ሊያዝ ይችላል።
2. በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ስለንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘውም ገቢ የተመለከቱ ኃይለ ቃሎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው ።

<u>አንቀጽ 282 የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎች</u>

የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎችን አሳዳሪው ግዴታ ሊገባባቸው አይችልም ።

<u>አንቀጽ 283 ስለወላጆች ሥልጣን</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሳዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሳዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ ።
2. አባት እና እናት ያለመግባባታቸውን በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ከሁለቱ አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አባትና እናት በአሳዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም።

<u>አንቀጽ 284 የወላጆች መለያየት</u>

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሳዳሪነቱ ስልጣን የአንደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የአሳዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን ወደላይ የሚቀጠሩ

ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ::

<u>አንቀጽ 285 አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ</u>

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ በልጁ አስተዳደግ ረገድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ከወላጆቹ አንዳቸው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል::

<u>ንዑስ ክፍል 2</u>

<u>አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር</u>

<u>አንቀጽ 286 መሠረቱ</u>

1. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል::
2. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስከበርና በማስተዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት::

<u>አንቀጽ 287 የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት (1) ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከጀመረ በኋላ</u>

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነቱን ሥራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሦስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል፣ የዋጋውንም ግምት ያወጣል::
2. ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው ዕዳ ሲኖር በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካላስፈረው በስተቀር የዕዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል::

<u>አንቀጽ 288 (2) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት</u>

1. .አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆኖ ወርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሶስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል ፣ የዋጋውንም ግምት ያወጣል::

2. ሞግዚቱ ከውርስ ሀብት ውስጥ ድርሻ ያለው እንደሆነ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል፡፡

3. የንብረት ቆጠራው ባለመከናወኑ ወይም በአግባቡ ባለመሠራቱ ለሚደርስ ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅበታል፡፡

## አንቀጽ 289 የሞግዚቱ ንብረት አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ስለሚቀላቀልበት ሁኔታ

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት ከግል ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡
2. በተለይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገንዘብ ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂሣብ ማስቀመጥ ወይም እንዲቀ መጥ ማድረግ አይፈቀድለትም፡፡

## አንቀጽ 290 የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ውድ ዕቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ

አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር የገንዘብ ሰነዶችን ፣ ውድ ዕቃዎችን ፣ ጠቃሚ ጽሑፎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ ሞግዚቱ ሊጠፉ ወይም ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ሥፍራ ማስቀመጥ አለበት፡፡

## አንቀጽ 291 የፍርድ ቤት ሥልጣን

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚቱ የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ መመሪያ እንዲሰጥ የልጁ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዳቸው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

2. ፍርድ ቤቱም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ የሞግዚቱን ችሎታና የልጅየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን መመሪያ ይሰጠዋል::

## አንቀጽ 292 አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ንብረት የሚያስተላልፍ ሰው የንብረቱን. አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሠራር መመሪያዎች ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዝ ይችላል::
2. የአሠራር መመሪያዎቹን ተከትሎ ለመስራት የማይቻል ወይም አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስበት መስሎ የታየው እንደሆነ ሞግዚቱ መሪያዎቹ እንዲስተካከሉለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል::

## አንቀጽ 293 ስለንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መሰል ድርጅቶች

1. የንግድ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆነ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤት ሊያዘው ይችላል::
2. ፍርድ ቤቱ ይህንን ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትነቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ የሞግዚቱን ችሎታና አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት::

## አንቀጽ 294 አንዳንድ ንብረቶችን ስለመሸጥ

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን አክስዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ለመሸጥ ይችላል::

2. በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጩ እንዳይካሄድ ለመከልከል ይችላል::

## አንቀጽ 295 ለአምጪው እንዲከፈል ስለሚሉ ሰነዶች

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለአምጪው እንዲከፈል የሚሉ ሰነዶች የልጁ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በተመዘገቡ ሰነዶች እንዲለወጡ ማድረግ አለበት::
2. ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ግዴታ ነፃ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል::

## አንቀጽ 296 ዕዳዎችና ገቢ ገንዘቦች

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕዳዎች ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል::
2. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታል እና ሌላ ገቢ ይቀበልለታል ፡ ስለመቀበሉ በማረጋገጥም ደረሰኝ ይሰጣል::

## አንቀጽ 297 ካፒታልን አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ስለማዋል (1) የሞግዚቱ ግዴታ

1. የገንዘቡ መጠን ከ500 ብር በላይ የሆነ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ካፒታል ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ማዋል አለበት::
2. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል::

## አንቀጽ 298 (2) የጊዜ ገደብ

1. ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሶስት ወራት ውስጥ በአትራፊ ሥራ ላይ መዋል አለበት::

2. ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል::

አንቀጽ 299 ኃላፊነት

1. በአትራፊ ሥራ ላይ ላላዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ ሕጋዊ ወለዱን አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መክፈል አለበት::
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊፈረድበት ይችላል::

አንቀጽ 300 ገቢዎች

1. አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች ገቢዎቹ በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆንም ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲውል ሞግዚቱ ለአሳዳሪው ይሰጠዋል::
2. ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር ለዚህ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሳዳሪው ይከፈላል::
3. የአከፋፈሉ ሁኔታ በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሠረት ሊሻሻል ይችላል::

አንቀጽ 301 የኪራይ ውሎች

በፍርድ ቤት ፈቃድ የተደረጉ ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ የሚያደርጋቸውን የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለመጠን ከደረሰ ከሶስት ዓመታት በኋላ እንዲፈጽማቸው አይገደድም::

አንቀጽ 302 ስለውርስ

1. ልጁ በውርስ የሚያገኘው ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል::
2. ሞግዚቱ የውርሱ ሀብት ዕዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ውርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም::

አንቀጽ 303 ስለ ስጦታ

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የለውም በማለት ካልሆነ በስተቀር ሞግዚት አል ቀበልም ለማለት አይችልም::

2. በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጪ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ ለመስጠት አይችልም።

## አንቀጽ 304 የዋስትና ግዴታ መግባት የማይቻል ስለመሆኑ

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው ዕዳ በዋስትና ሊያሲዝ አይችልም።

## አንቀጽ 305 ስለ ግልግል

ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከ1 ሺህ ብር ያነሰ ካልሆነ ወይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ አይችልም።

## አንቀጽ 306 ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች

1. ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት በኪራይ ለመጠ ቀም ወይም ሌላ ማናቸውንም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈፀም አይችልም።
2. እንዲሁም ሞግዚቱ በፍርድ ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ማናቸውንም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም።

## አንቀጽ 307 ስለብድር

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም።

## አንቀጽ 308 አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈለጉ

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜ ከ14 ዓመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ የልጁ ዕድሜ በሚፈቅድለት

መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት።

2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም።

<u>አንቀጽ 309 ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እንዲሠራ ስለሚሰጠው ፈቃድ (1) መሠረቱ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕድሜና የገንዘብ አቅም መሠረት በማድረግ የዕለት ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።
2. ይኸው ፈቃድ በዝምታም ሊሰጥ ይችላል።

<u>አንቀጽ 310 (2) የዕለት ጉዳዮች</u>

1. ድርጊቱ እንዲፈፀም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ በምንም መንገድ የዕለት ጉዳይ ሊባል አይችልም።
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከ300 ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ድርጊቱ የዕለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም።

<u>አንቀጽ 311 (3) በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት</u>

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎች ሞግዚቱ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስ ነው።

<u>አንቀጽ 312 ኑዛዜ</u>

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም ኑዛዜ ሊያደርግ አይችልም።
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ 16 ዓመት ሳይሞላው ኑዛዜ ማድረግ አይችልም።
3. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ 16 ዓመት ሳይሞላው የሚያደርገው ኑዛዜ 16 ዓመት ከሞላው በኋላ ባይሰርዘውም ውጤት አይኖረውም።

<u>አንቀጽ 313 ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚት ስለሚያደርገው ወጪ</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲል ከግሉ የሚያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት መብት አለው።

**አንቀጽ 314 አካለመጠን ስላልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ**

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታና ሂሣቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።
2. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ሲያቀርቡለት ሞግዚቱ የአስተዳደርና የሂሳብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ያደርጋል።

**አንቀጽ 315 ተፈፃሚነት**

በዚህ ህግ ከአንቀጽ 281 እስከ 283 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሞግዚትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ክፍል 4
## አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት
### ንዑስ ክፍል 1
### አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች

**አንቀጽ 316 መሠረቱ**

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የሚፈጽማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሽ ይሆናል።

**አንቀጽ 317 እንዲፈርስ ስለመጠየቅ**

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወይም ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ናቸው።

**አንቀጽ 318 ስለተዋዋዩ ቅን ልቦና**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 316 የተደነገገው ቢኖርም ሌላው ተዋዋይ ወገን ከልጁ ጋር የተዋዋለው ይህንን እንዲ

ያደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቦና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል::

2. ሌላው ተዋዋይ በልጁ አላዋቂነት የተጠቀመ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ተፈፃሚነት አይኖረውም::

አንቀጽ 319 ስለሚመለስ ገንዘብ

1. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ቀን በልጅጉ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል::
2. ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለመመለስ አይገደድም::

አንቀጽ 320 ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ (1) መሠረቱ

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሕገወጥ በሆኑ ሥራዎች ያለአግባብ የበለፀገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል::

አንቀጽ 321 (2) አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ማለት

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳን ይህን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብት አያ ጣም::
2. እንዲሁም አካለመጠን ደርሻለሁ ማለቱ ከውል ውጪ የሆነ ኃላፊነትን የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆ ጠርበትም::

ንዑስ ክፍል 2
የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች

አንቀጽ 322 በደንብ ስለተፈፀሙ ድርጊቶች

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ልጁ አካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንደ ፈፀማቸው ተቆጥረው በኃላፊነት ያስጠይቁታል::

2. ሞግዚቱ በኃላፊነት እጠየቅበታለሁ ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በሕግ መሠረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስ ተቀር አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈፀማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ኃላፊ አይሆንም።

አንቀጽ 323 የሕግ ድንጋጌዎችን ስለመተላለፍ

የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈፅማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 324 ስለ ሦስተኛ ወገኖች

1. ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የተሰጠውን መመሪያ ሶስተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።
2. አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ንብረቱን የሰጠ ፣ የተናዘዘ ወይም የተወ ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ 325 ስለምትክ ሞግዚት

በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ንዑስ ክፍል 3

## በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

አንቀጽ 326 ስለሞግዚት

1. ሞግዚቱ በፈፀመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለማክበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈፀሙ አካለመጠን

ባልደረሰው ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## ክፍል 5
## አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

### አንቀጽ 327 ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው

ሀ) አካለመጠን ሲደርስ ወይም

ለ) ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይውጣ ሲባል ነው::

## ንዑስ ክፍል 1
## ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

### አንቀጽ 328 ጋብቻ

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በዚህ ሕግ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይወጣል::

### አንቀጽ 329 በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ 14 ዓመት ሲሞላው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ መጠየቅ ይችላል::
2. ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት የልጁን ሁኔታና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክ ንያት ተመልክቶ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መሆኑ ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል::

<u>አንቀጽ 330 ውጤቶች</u>

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ በሕግ አካለመጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል።

<u>አንቀጽ 331 የማይሻር ስለመሆኑ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲሆን የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም።
2. በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የመሆን ሁኔታ ጋብቻው ቢፈርስም እንኳን ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው የፈረሰው በጋብቻ የተፈቀደው ሕጋዊ ዕድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከሞግዚት አስ ተዳደር ነፃ መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤት ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል።

<u>ንዑስ ክፍል 2</u>

<u>የሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ</u>

<u>አንቀጽ 332 መሠረቱ</u>

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራው ሲያበቃ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳደረው ሰው ወይም ለወራሾቹ ያስተዳደረበትን ሂሣብ ማቅረብ አለበት።
2. እንዲሁም በሞግዚትነት ያስተዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ፣ የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው ዕዳዎች ካሉም ማስታወቅ አለበት።

<u>አንቀጽ 333 የንብረቶች በመዝገብ አለመግባት</u>

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠው የንብረቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ቸል ያለ እንደሆነ

የልጁን ንብረት በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይቻላል።

2. ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ምስክሮች በሚሰጡት ቃል አንድ ንብረት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።

<u>አንቀጽ 334 ሂሣቦችን ስለማፅደቅ</u>

1. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ የሞግዚቱን ሥራ ሂሣቦች ያጸደቀ እንደሆነና ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላው ከሆነ ሂሣቦቹን ካጸደቀ በኋላ እስከ አንድ ዓመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሣብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል።
2. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ ሂሣብ እንዳያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
3. አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ አካለመጠን የደረሱ ሲወርሱት እነዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሣብ ያፀደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሣብ ከማቅረብ ነፃ አውጥተውት እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም።

<u>አንቀጽ 335 ስለ ይርጋ</u>

1. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፣ ወኪሎቹ ወይም ወራሾቹ በሞግዚትነት ሥራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለኃላፊነት የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ክሶች ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከተወበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳሉ።
2. ሆኖም አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶቹ እን ዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለከልም።

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 336 ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. በ1952ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ

   ሀ. ስለ ሰዎች ከሚለው አንደኛ መጽሐፍ ውስጥ ከአንቀጽ 198 - 338፣

   ለ. ስለ ቤተ ዘመድና ስለውርስ ከሚለው ሁለተኛ መጽሐፍ ውስጥ ከአንቀጽ 550 - 825፣

   ያሉ ድንጋጌዎች በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

2. ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ፣ መመሪያዎች ፣ ውሳኔዎችና የአሠራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

### አንቀጽ 337 በቀድሞ ሕጎች መሠረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች

1. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ ሕጋዊ ሁኔታዎችን ለማስገኘት አዲሱ ሕግ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳን በቀድሞው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ፀንተው ይቀጥላሉ።
2. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ያስገኟቸውን ውጤቶች ይህ ሕግ አይለውጣቸውም።

### አንቀጽ 338 ስለምዝገባ

1. የክልሉ መንግሥት ይህ ሕግ በሥራ ላይ በዋለ ባጭር ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ሕግ ያወጣል አስፈላጊ ተቋም ችንም ያደራጃል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የክብር መዝገብ ሹም ጽሕፈት ቤት ተቋቁሞ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ሕጉ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው መስተዳድሮች አግባብ

ባለው አካል የተሰጠ ወይም የሚሰጠ የልደት ፣ የጋብቻና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹሙ እንደተሰጠ ሰነዶች ተቆጥረው ሕጋዊነት ይኖራቸዋል ::

## አንቀጽ 339 በእንጥልጥል ስላሉ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች

1. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት የተያዙ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች በዚህ ሕግ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ::
2. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ሕግ መሠረት በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ የተያዙ የፍቺ ክርክሮች በሙሉ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን ወዳላቸው ፍርድ ቤቶች ይተላለፋሉ::
3. ፍርድ ቤቶችም እነዚህን ጉዳዮች ተረክበው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ውሳኔ ይሰጣሉ::
4. ይህ ሕግ ከመውጣቱ በፊት በቀድሞ የቤተሰብ ሕግ መሠረት የተፈፀሙት ጉዳዮች በዚህ ሕግ መሠረት እንደተፈፀሙ ተቆጥረው ይቀጥላሉ::

# የኦሮሚያ ክልል ቤተሰብ ሕግ

## ማውጫ


| ርዕስ | | ገጽ |
|---|---|---|
| የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ | | 1 |
| | **ምዕራፍ አንድ** | |
| | ስለዝምድና | 5 |
| | **ምዕራፍ ሁለት** | |
| | ስለመተጫጨት | 7 |
| | **ምዕራፍ ሦስት** | |
| | ስለጋብቻ አፈፃፀም | 9 |
| ክፍል አንድ | ጠቅላላ | 9 |
| ክፍል ሁለት | ጋብቻን ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች | 10 |
| ክፍል ሦስት | ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም | 13 |
| ክፍል አራት | ስለጋብቻ አፈጻጸም | 15 |
| ክፍል አምስት | ስለጋብቻ ምዝገባ | 17 |
| | **ምዕራፍ አራት** | |
| | የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት | 18 |
| | **ምዕራፍ አምስት** | |
| | የጋብቻ ውጤት | 20 |
| ክፍል አንድ | ጠቅላላ | 20 |
| ክፍል ሁለት | ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት | 22 |
| ክፍል ሦስት | ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት | 24 |
| | **ምዕራፍ ስድስት** | |
| | በጋብቻ ውስጥ የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን | 29 |
| ክፍል አንድ | ጋብቻ ለመፈጸሙ ወይም የሚጸና ጋብቻ ስለመኖሩ ስለሚቀርብ ክርክር | 29 |
| ክፍል ሁለት | ከፍቺ በመለስ ያሉ ክርክሮችን ስለመወሰን | 31 |
| | **ምዕራፍ ሰባት** | |
| | የጋብቻ መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት | |
| ክፍል አንድ | ጠቅላላ | 31 |
| ክፍል ሁለት | በስምምነት ስለመፋታት | 32 |
| ክፍል ሦስት | ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ | 34 |
| ክፍል አራት | የባልና ሚስት ሀብት ስለማጣራት | 38 |

ክፍል አምስት የክርክሮች ሂደትና አወሳሰን........................................ 41

## ምዕራፍ ስምንት

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት
አብሮ ስለመኖር.................................................. 43

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ስለመወለድ................................................................ 47
ክፍል አንድ አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ.............................. 47
ንዑስ ክፍል አንድ አጠቃላይ ድንጋጌዎች.............................. 47
ንዑስ ክፍል ሁለት አባትነት በህግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ............ 47
ንዑስ ክፍል ሦስት ልጅነትን ስለመቀበል.................................... 49
ንዑስ ክፍል አራት በፍርድ ቤት ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ
ስለማድረግ.............................................................. 51
ክፍል ሁለት አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት......... 53
ክፍል ሦስት ስለልጅነት ማስረጃ.......................................... 55
ክፍል አራት በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለመካድ.................. 57
ንዑስ ክፍል አንድ በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር......................... 57
ንዑስ ክፍል ሁለት ስለመካድ.................................................. 58

## ምዕራፍ አስር

ስለጉዲፈቻ.............................................................. 61

## ምዕራፍ አስራ አንድ

ቀለብ ስለመስጠት ግዴታ................................................. 67

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች........................................... 71
ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች........................................ 71
ክፍል ሁለት አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች........... 72
ክፍል ሦስት የአሳዳሪውና የሞግዚት ሥልጣን.................................. 82
ንዑስ ክፍል አንድ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ.......... 82
ንዑስ ክፍል ሁለት አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር.. 85
ክፍል አራት አካለ መጠን ያልድረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን
ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት................................. 92
ንዑስ ክፍል አንድ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ስራዎች....................... 92
ንኡስ ክፍል ሁለት የሞግዚት ሕጋዊ ድርጊቶች................................. 93
ንዑስ ክፍል ሦስት በሐላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች............. 94
ክፍል አምስት አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ........ 95
ንዑስ ክፍል አንድ ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ስለመውጣት...................... 95
ንኡስ ክፍል ሁለት የሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ............... 96

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች..................................................... 98